# ይድረስ ለሌ/ጄኔራል ፃድቃን ገብረ-ትንሳይ

***(ወተንጎ (ዛፍ ቆራጩ)***

September 1, 2018

ውድ ጄኔራል፣ በቀደም ዕለት፣ ሃገር ቤት ለሚታተመው አዲስ አድማስ ሳምንታዊ ጋዜጣ የሰጡትን ቃለ-መጠይቅ ደጋግሜ በጥሞና አነበብኩት፡፡ በበኩሌ እርስዎ በየጊዜው ሀገር ውስጥ ያሉ የብዙሃን መገናኛ ዘዴዎችን ተጠቅመው ለህዝብ በሚያስተላልፉት አስተያየት እደመማለሁ፡፡ ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡ የአንድ ሰው ሃሳብ በሌላው ዘንድ ተወደደም፣ ተጠላም መደመጥ ወይንም መነበብ አለበት፡፡ ማንም ሰው የተሰማውንና የመሰለውን መናገርና መፃፍ መብቱ ነው፡፡ እኔም ይሄን የእርስዎን ቃለ-መጠይቅ ተመርኩዤ የራሴን ሀሳብ ለማንሸራሸር ፈለኩና ይህችን መጣጥፍ ልሞነጫጭር በቃሁ፡፡
ከሁሉም በቅድሚያ ግን አንድ የምወደውን ዘፈን ልጋብዝዎት፡፡ ይህን እጅግ ድንቅ የሆነውን የሀገራችንን የቆየ ዘፈን የሚያቀነቅነው እውቁና የምንወደው ኢትዮጵያዊው ጥላሁን ገሠሠ ነው፡፡ ጥልዬ እንዲህ ብሎ ነበር የዘፈነው…

‹‹… አይነቅዝም ዝምታ ቢለኝም ተረቱ፤

አፍርጬው ልናገር ይብራራ…ን እውነቱ፡፡

የመኖር ትርጉሞች ማወቅ ስለሚሹ፤

የስንፍና ጭጋግ ይከፈት ግርዶሹ፡፡…››

ድንቅ ነው! ወደ ነገሬ ልመለስ… እኔ በነሐሴ 12፣ 2010 ከሰጡት ቃለ-መጠይቅ የተረዳሁት አንድ አብይ ቁም ነገር አለ፡፡ ይኸውም ድሮ እርስዎና ጓደኞችዎ ትግራይን ነፃ ለማውጣት በሚል የተማማላችሁበትን ሻጋታ የትግል ከታብ አሁንም ከተቆለመመ አንገታችሁ ላይ ያላወለቃችሁት መሆኑን ነው፡፡ ዛሬም ኋላ በቀረ የጎሳና የብሄር ጠያፍ አስተሳሰባችሁ ላይ ተጣብቃችሁ ቀርታችኋል፡፡ በቁረጠው-ፍለጠው፤ በአናክሰው-አጋጨውና በእኛው ብቻ እንብላው የተሰናሰለ የክፉት ፖለቲካችሁን አሁንም ለመተው እንደማትፈልጉ ነው የተረዳሁት፡፡ ክፉ አባዜ! ያልታደልሽ እንዴት አደርሽ… ዓይነት ሆነና ዘለለት እርስዎን ባነበብኩዎት ቁጥር የምረዳው ይሄንኑ ነው፡፡ እስኪ በማስረጃ ላጫውቶት፡፡ (ልወጥሮት ነው የሚለው ያ የምትጠሉት የአዲስ አበባው አራዳ ወገኔ!)
በቃለ-መጠይቅዎት ላይ፣ ‹የትግራይ ህዝብ ዒላማ ተደርጎ እየተጠቃ ነው፣› በሚል ጣና በለስ ላይ የተፈጸመውን የግድያ ወንጀል (እውነት ከሆነ) እንደማስረጃ በማቅረብ ኮንነዋል፡፡ በርግጥም ተፈጸመ የተባለው ግድያ ሊወገዝ የሚገባው ከባድ ወንጀል ነው፡፡ ሰላም ወዳዱ የክልሉና የኢትዮጵያ ህዝብም ይሄንን ውጉዝ ከመ-አርዮስ የሆነ ድርጊት በእጅጉ ይጠየፈዋል፡፡ አዎን፣ ሰው ነኝ የሚልና፣ በሰብዓዊነት የሚያምን ሁሉ ይህ ዓይነቱን ግፍ በፍፁም አይፈልገውም፡፡ ማንም ኢትዮጵያዊ በማናቸውም የሃገሪቱ (ይቅርታ የኢትዮጲያ) ክልል ተዘዋውሮ መኖርና መስራት ይገባዋል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ይሄ ስሞታዎት አንካሳ ሆኖ ታየኝ፤ ወደ አንድ ወገን ያጋደለ ሸውራራ ብሶት! ላብራራው፡፡ ባለፉት 27 ዓመታት እርስዎና የትግል አጋርዎችዎ ያጎናጠፉን ዋንኛው ነገር ቢኖር በየፈለግንበት መዘዋወር ሳይሆን፣ መሰደድ፣ መኖር ሳይሆን፣ መፈናቀል፣ መከበር ሳይሆን፣ መታሰርና መገደልን ነው፡፡ ይሄ ደሞ በተለይም እርስዎና ድርጅትዎ ሕውሓት የመሳሪያ ቃታ ያነጣጠራችሁበትና ገጀራ የሳላችሁለት ምስኪኑን የአማራ ሕዝብ በተለየ ሁኔታ የሚመለከተው ጉዳይ ሆኖ ቆይቷል፡፡ በ1968ቱ የጫካ ማኒፌስቷችሁ በሚያስተዛዝብ ሁኔታ አማራውን ጠላታችሁ አድርጋችሁ መፈረጃችሁ ዓለም ያወቀው ፀሐይ የሞቀው ሃቅ ነው፡፡ ባለፉት 27 የመከራ ዘመናት አማራው፤ ሴት፣ ሕፃን፣ አዛውንትና አቅመ-ቢስ ሳይባል፤ ከተለያዩ ክልሎች በገፍ ተፈናቅሏል፣ ተግዟል፣ ተሰዷል፣ ታስሯል፣ ከገደል አፋፍ ላይ የናዳ ያህል ተወርውሯል፣ እንደ ጌታ እየሱስ ክርስቶስ በየዛፉና በየቤቶች ታዛ ስር ተሰቅሏል፣ ንብረቱን ተነጥቋል፤ በአሰቃቂ ሁኔታ ተጨፍጭፏል፤ ብሎም ተገድሏል፡፡ ያን ጊዜ የእናንተ መልስ ምን እንደነበር ያስታውሱታል፡፡ ሟቹ ጠ/ሚ፣ ‹ሞፈር ዘመት… ደን

አውዳሚ፣› እያለ አልነበረም እንዴ እነዚያ ምስኪን አማራ ኢትዮጵያዊ ዜጎች ላይ ሲያላግጥ የነበረው! ይሄንን ሀገር ያወቀውንና ፀሐይ የሞቀውን ጉዳይ እንዴት ልንረሳው እንችላለን!

በቅርቡም ኦሮሞዎች፣ ጌድዎች፣ ሶማሌዎችና ወላይታዎች ከየኖሩበት ተፈናቅለዋል፣ ተሰደዋል፣ ተገድለዋል፡፡ የእናንተ ትግልና ሕገ-መንግስት የመጨረሻ ውጤት ይሄ መሆኑን ከቶም እንዳይረሱ! ይሄ ሁሉ የእናንተ ድብቅ ተንኮላችሁ፣ እርስዎና መሰልዎችዎ በተለየ ሁኔታ (በማስመሰል) የምትቆረቆሩለትን የትግራይ ሕዝብ የጨርቁን ጫፍ ያህልም አልነካው፡፡ እርስዎ እንደ አንድ የተማረ ዜጋና ባለስልጣን የሰዉን ወይም የመላውን ዜጋ አጠቃላይ መፈናቀል፣ መሰደድ፣ መታሰርና መገደል ማውገዝ ሲገባዎት፣ ወደ አንድ ወገን ብቻ ማድላትዎ ትዝብት ውስጥ ይከትዎታል፡፡ እንዴት ተደርጎ ነው የዚህ ዓይነት ጠባብ አመለካከት የተጣባው አንድ ግለሰብ ይህችን ሃገር (ይቅርታ ኢትዮጰያን) በኤታማዦር ሹምነት ሲያስተዳድር የነበረው! የጉድ ሃገር አሉ! በሌላም በኩል ይሄ የእርስዎና የመሰሎችዎ ቡድንተኝነት የሚያስገነዝበን ነገር ቢኖር፣ ያኔም የኢትየጵያን ሕዝብ በፍትሃዊነትና በእኩልነት እንዳላገለገላችሁት ነው፡፡ ለነገሩ በየቦታው በሃላፊነት የተሾሙት የትግል አጋሮችዎ በጋጠ-ወጥነትና በጠባብ ዕይታ እየሰሩት ያለው ጭፍን ወገናዊነት ነው ሲያማርረን፣ ሲያበሳጨንና ሲያስለቅሰን የኖርነው፤ መኖር ከተባለ፡፡

ይህችን ሃገር በከፍተኛና ወሳኝ የስልጣን ማማ ላይ ሆነው በፍትሃዊነት፣ በእኩልነትና በታማኝነት እንዲያገለግሉ አደራ የተጣለብዎት አንድ ግዙፍ ጄኔራል ስለአንድ ወገን ብቻ በሸውራራ እይታ በአስመሳይነት እየተቆረቆሩና እየጮሁ ወደ ጎሳ አቋማዳዎት እንደ ቀንድ አውጣ ተመልሰው ሲሸሸጉ ሳይ በጣም አፍርልዎታለሁ፡፡

ስለትግራይ ሕዝብ ኢትዮጵያዊነት እርስዎ ብቻም ሳይሆኑ ሁሉም ያውቀዋል፡፡ አዎ፣ የትግራይ ህዝብ ኢትጵያዊ አንድነቱን ይወደዋል፤ ያምንበታልም፡፡ ይሁን እንጂ፣ ሕገ-መንግስቱ እንደብቸኛ አማራጭ ተደርጎ በእርስዎ ዘንድ መገለጡ ግርምታን ይፈጥርብኛል፡፡ ለመሆኑ የትግራይ ሕዝብ ከዚህ ሕገ-መንግስት በፊት በኢትዮጵያዊነት ከሌላው ሕዝብ ጋር አንድ ሆኖ አልኖረም እያሉን ነው እንዴ? መቼም ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም! የሆነስ ሆነና፣ ይሄ እርስዎና መሰልዎችዎ የሚኩራሩበት ሸውራራ ሕገ-መንግስት መነካት የለበትም በሚል ያዙኝ ልቀቁኝ ዓይነቱ የተለመደ ማስፈራሪያችሁ ማለቂያው የት ላይ ይሆን? ‹አንቀፅ 39 አይነካም፤ ዋስትናችን ነው፣› እያሉ ሌላውን መቀስቀስ በሚመስልብዎ ሁኔታ እየተናገሩ እንደሆነ ይታወቅብዎታል፡፡ የትግራይ ሕዝብ፣ ‹‹...ኢትዮጵያዊነት ከደሙና ከአጥንቱ ጋር የተዋሃደ ነው...›› ይሉናል፡፡ ይሄ ከሆነ ታድያ አንቀጽ 39 በዋስትና ስም በሕገ-መንግስቱ ውስጥ የሚቀመጠው ለምንድን ነው? የሚገርመው ደሞ፣ ይሄንን ሁሉ ካሉ በኋላ፣ ‹‹...ሕገ-መንግስቱ በስርዓተ-አልበኝነት ጫጫታ ሳይሆን፣ በስርዓቱ እንዲታይ፣ መሻሻል ካለበትም መሰረቱን ሰብአዊ መብትና ዴሞክራሲን እንዲሁም የብሔር ፌዴራሊዝምን ታሳቢ አድርጎ ... እንዲሻሻል...›› በማለት ትዕዛዝ በሚመስል ቃና ይናገራሉ፡፡ አካሄድዎ ለሁላችንም በጅምላ የማይገባን መስሎዎት ከሆነ እጅግ ተሳስተዋል፡፡ ይኸውሎት፣ የኢትዮጵያ ህዝቡ (እንደለመዳችሁት የትኛው ሕዝብ የሚል ደካማ ክርክር ካልደነቀሩ በስተቀር...) የብሄር ፌዴራሊዝም አላዋጣንም፤ ይፈተሽ እያለ ነው፡፡ ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ መበዝበዝ፣ ለኢ-ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ፣ ለጭቆና፣ ለእርስበርስ መገዳደል፣ ለጥቂቶች (የእናንተ) የብቻ ስልጣንና የንብረት ጥቅም ማጋበሻ፣ ለብዙሐኑ መደፍጠጫና ማቆርቆዣ ዓይነተኛ ምክንያት ስለሆነ ሊፈተሽ ይገባዋል እየተባለ ነውና መልስዎ ምን ሊኾን ነው? መገንጠል? ያም የሚያዋጣ ከሆነ መሞከር ነው፡፡ (ይቅርታ መንገዱን ጨርቅ ያድርግልዎት አላልኩም፡፡) ይሄ ዓይነቱ የእብደት አካሄድ ግን በማንኛውም ሰላምንና አንድነትን በሚወድ ኢትዮጵያዊ አይመከርም፡፡

ይሄ የብሄር ፖለቲካም አይደለ እንዴ እርስዎንና መሰልዎችዎን በጠባብነት (ለቋንቋዬ ይቅርታ) እንድታስቡ፣ እንድታብጡ ወይም አቅላችሁን እንድትስቱ የሚያደርጋችሁ፡፡ እሱም አይደል እንዴ ሀገር ምሩ ስትባሉ፣ ለጎጣችሁ ብቻ እንድታስቡ ያደረጋችሁ... አገር ጥቀሙ ስትባሉ ጎጣችሁን ብቻ እንድታገለግሉ የሚያደርጋችሁ... ድርጅት አስተዳድሩ ስትባሉ ወደ ክልላችሁ ብቻ አንድታደሉ የሚያደርጋችሁ... ከአዲስ አበባና መሐል ሃገር እያኘካችሁ ወደ ትግራይ የሚያስውጣችሁ ይሄ የከፋት ፖለቲካችሁ አይደለም ወይ! ነገራችሁ ሁሉ የኛ ‹ወገን› ተነካ ብቻ! ይሄ በሕዝብ ስም የምታደርጉት የሐሰት መቆርቆር ሽፋን እንጂ፣ ለራሳችሁ ብቻ ብላችሁ የምታነሱት ሰበብ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ግን ለምንድን ነው ለሌላው ህዝብ የማታስቡት? (ለነገሩ ጠባቦች እንደዚህ ተብለው አይጠየቁም ለካ!) የጎሳ ፖለቲካን ስትጀምሩት፣ ይጠቅመናል ብላችሁ ነበር፡፡ ግን ደሞ ይሄ አካሄዳችሁ ለራሳችሁና ብሎም ለሃገር እንደማይበጅ ሲነገራችሁና እዘጊዎ ሲባል ትስቁ ነበር፡፡ አሁን ላይ ግን ጥቅማችሁ ሲነካ ወይም ሊነካ መስሎ ሲታያችሁ ጫጫታና ሆይ ሆይታ አበዛችሁ፡፡ ‹የወረወርኩት አንካሴ ተመልሶ በራሴ፣› ይልዎታል ይሄ ነው፡፡ ‹እኛም ነግረናል ሃገር ይቃጠላል ብለናል፣› አለች አሉ ሴትዮዋ!

ክቡር ጄኔራል፣ ይሄንን የጫካ ማኒፌስቷችሁን በሕገ-መንግስት ስም ሕዝብ ላይ ካልጫንን እያላችሁ ማስፈራራታችሁን ካላቆማችሁና ከክፉ ተግባራችሁ ባስቸኳይ ካልታቀባችሁ፣ አደጋው የከፋ ነው፡፡ ለሁላችንም አይበጀንም፡፡ ሌላው ቢቀር ባለፉት 27 ዓመታት ያካበታችሁትን እጅግ የበዛ የየግልና የየጋራ ንብረቶቻችሁን ያሳጣችኋል ወይም ያወድምባችኋል፤ ሕይወትንም ያጠፋል፡፡ ደሞስ ለመሆኑ፣ ይሄ የእርስዎ ሕገ-መንግስት ሲረቀቅና ሲፀድቅ ስንቱ ኢትዮጵያዊ ነው የተሳተፈው? ሁሉን አካታች እንዳልሆነስ ከአርቃቂዎቹ ግለሰቦች እየተነገረን አይደለም እንዴ! ሃገሪቱ በክልል ስትከፋፈል ከፍተኛ ሚና የተጫወቱት ባንድ እጅ ጣት የሚቆጠሩ ግለሰቦች እነማን እንደነበሩ የማናውቅ ይመስልዎታል! የአማራው ሕዝብ በተወካዩ ተሳትፎ ነበር እንዴ? የሲዳማውስ? የአፋሩስ? የወላይታውስ? እነዚህና ሌሎችም ዜጎች በሃገራዊ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ እንዳልተወከሉ የታወቃል፡፡ የአማራውን ዙሪያ ክልል እየበጣጠሳችሁ ከትግራይ ጋር ስትቀላቅሉ አንድም የአማራ ተወካይ በመሀላችሁ አልነበረም፡፡ ብዙ፣ እጅግ ብዙ፣ ግፍ-አዘል ጉዳዮችን ማንሳት ይቻላል፡፡ እነዚህንና መሰል ሃገር አውዳሚና ትውልድ ጨራሽ ድርጊቶችን የማናውቅ መስሎት ከሆነ፣ እጅግ ተሳስተዋል፡፡ በዚህ ዓይነት ለጠፍጥፈህ፣ ለበጥብጠህና በጣጥሰህ ግዛ የሚመቸው ሕገ-መንግስታችሁ እንዴት እንደመጣና እንደተጫነብን መላው የኢትዮጵያና የዓለም ሕዝቦች አሳምረን እናውቃለን፡፡ አጠቃላይ የኢተዮጵያ ሕዝብ ባልመከረበትና በተሳትፎ ባላፀደቀበት ሁኔታ የጫካ ማኒፌስቶን ሕገ-መንግስት አድርጎ አገር ትመራበት ማለት የትም አያደርስም፡፡ ይሄ አሰቃቂና በየትም ሃገር ያልታየ እጅግ ከባድ ግፍ ነው፡፡ የእስካሁኑን የሰቆቃ ኑሯችንን ምሬት በተሞላበት ትዕግስት አልፈነዋል፡፡ ይሄ ያለፈው የግፍ፣ የኢ-ፍትሃዊና የጭቆና አገዛዝ ከእንግዲህ ወዲያ እንደማይቀጥል ግን ልታውቁት ይገባል፡፡ የልቁንም ሁሉንም አካታች በሆነና በሚያስማማ መልኩ ሕገ-መንግስቱ እንደገና ሊከለስና ሊስተካከል ይገባል፡፡

<<…የትግራይ ሕዝብ ከፈለገ ሕውሓትን ያጎለብታል፤ ካስፈለገው ደሞ ይገለዋል፡…>> ይሉናል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብስ የሚለው ይሄን አይደል! እግሩን ለጠጠር ግንባሩን ለጥይት ሰጥቶ ደርግን ገረሰሰ የተባለለት የትግራይ ሕዝብ ይሄንን ሁሉ መስዕዋትነት ከፍሎ ሲያበቃ፣ ጥቂት ወሮበሎችን ለሕግ አሳልፎ ሳይሰጥ በጉያው አቅፎ ማስቀመጡ ሁላችንንም ያስቆጨናል፡፡ እነዚህ ጥቂት ወሮበሎችና አሁን ወደ ባለሐብትነት የተለወጡ ዜጎች፣ ከደርግ የበለጠ ምን የሚያስፈራ ጡንቻ ቢኖራቸው ነው በትግራይ ሕዝብ ዘንድ የሚፈሩት? ደርግ የወደቀው በእናንተ ብቻ አይደለም፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ የላቀ ድጋፍም ጭምር ነው የተባለውን ስትቃወሙ የነበራችሁ ሰዎች አሁን እውነትነቱን እያረጋገጣችሁልን መሆኑም አስደስቶኛል፡፡ አይደለም፣ በጫካ ትግላችን ለብቻችን ነው ለድል የበቃነው የምትሉም ከሆነ፣ የጥቂቶች ጡንቻ ከደርግ የጦር መሳሪያ አቅም ጋር አይነጻጸርምና፣ ቶሎ ብላችሁ እነዚያን ሰዎች እጅ እጃቸውን በመያዝ ለህግ አስረክቧቸው፡፡ ይሄንን መልዕክት ደሞ ለትግራይ ሕዝብ ቢያስተላልፉልኝ/ቢሰብኩልኝ ማለፊያ ነው፡፡ እርስዎም ጉዳዩን በትብብር ቢመሩት ድንቅ ነው፡፡ ያለበለዚያ ይሄ የእኛ ሕዝብ፣ የትግራዩን ጨምሮ፣ የቢራ ፋብሪካውና፣ አንዲትም ጠብታ ላብ ሳያፈሱ ያካበቱት ያ ሁሉ ሐብት ስለሚያጓጓቸው ምንም ትንፍሽ አይሉም እያለ እንደሚቦጭቆት (እንደሚያማዎት) ፍጹም እርግጠኛ ይሁኑ፡፡

ውድ ጄኔራል፣ ቃለ-መጠይቅዎትን ጠለቅ ብዬ ሳነበው ለዚያ መከረኛ የትግራይ ሕዝብ የተላለፈ የ<መጡብህ… ተጠንቀቅ> ዓይነት ማስፈራርቾ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ እስኪ በማስረጃ ልወጥሮት… በቃለ-ምልልስዎ ላይ እንዲህ ይላሉ፤ <<…የጥላቻ መንገዱን ወደ አንድ አካባቢ በመግፋት… ሶማሌ ውስጥ የተደረገው ትግራይ ውስጥ ሊመጣ እንደሚችል… የሕዝብን መስዕዋትነት ማራከስ… መሐል ሃገር የሚደረገው ፀረ-ትግራይ እንቅስቃሴ… ትግራይ ሕዝብ ላይ ያነጣጠረ ፕሮፓጋንዳ… ወደ አንድ ሕዝብ ያተኮረ ጥላቻ…>>፡፡ እርስዎ እንግዲህ ይሄን ሁሉ የአናከሰው ንግግር የሚናገሩት ለውጡን እደግፋለሁ እያሉ ነው፡፡ ጥላቻ በጥቅሉ ማንም ሰው ላይ እንዳይደረግ ማስተማርና ማሳወቅ ሲገባ፣ ሚዲያን ወገናዊ በሆነ መልኩ ለፖለቲካ ፍጆታ መጠቀም በእጅጉ ያስተዛዝባል፡፡ በዚህ ዓይነት የትግራይ ሕዝብ ስጋት ውስጥ ወድቆ ለውጡን እንዳይደግፍ በአቋራጭ እየሰበኩ እንደሆነ ለማንም ግልጽ ነው፡፡ ከዚህም ባለፈ ሕዝቡ አመለካከቱን ከብዙሃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሳይሆን ወደ ጥቂቶቹ ጠባቦችና ጎጠኞች እንዲሆን የበኩልዎን አሳዛኝ ድርሻ እየተወጡ መሆኑን እገነዘባለሁ፡፡ የትግራይ ሕዝብ በሚታየው ሀገር-አቀፍ የለውጥ እንቅስቃሴ ተስፋ እንዲቆርጥ እንዲህ በማለት የነገር ዘገር እየነቀነቁ ያቀብላሉ፡፡ <<… በሕውሓት በራሱ ውስጥ የሃይሎች ፍትጊያ አለ፡፡ በአንድ በኩል አነስተኛ ቢሆንም ሪፎርም የሚፈልግ አለ፡፡… የትግራይ ወጣት ስርዓቱ እንዲስተካከል ሲጮህ የነበረው… በሕውሓት ስር ሆኖ ነው ይሄንን ለውጥ ማምጣት የፈለገው፡፡…>> (አጽንዖት በኔ) ስለዚህ፣ የእርስዎ አባባል ሲጠቃለል፣ <እኛን ጥቂቶቹን ለመገዳደር የሚበቃ ትግል በትግራይ ውስጥ የለም፤ ቢኖርም ጥቂትና ከሕውሓት ቁጥጥር የልወጣ ነው፡፡ ሕውሓት <<… 7 መቶ ሺህ ገደማ አባላት…>> ስላሉት ይሄንን መደርመስ ቀላል አይደለምና የትግራይ ሕዝብ አርፈህ ተቀመጥ፣> የሚል ነው፡፡

ጄኔራል፣ ይሄንን ለውጥ እደግፋለሁ ይበሉ እንጂ፣ በምን በምን ምክንያት እንደሚደግፉት ግልጥልጥ አድርገው አላስቀመጡልንም፡፡ ከኤርትራ ጋር የተጀመረው ግንኙነት ሕዝቡን አላሳተፈም በሚል ያጣጥሉታል፡፡ … የትግራይ ሕዝብ ሌላው ክልል ላይ ተገድሏልና ይህ ሁኔታ የለውጡ ስጋት ነው ይሉናል፡፡ … በርካታ በውጭ ሀገር መሰረታቸውን አድርገው ይንቀሳቀሱ የነበሩ ፓርቲዎች ወደ ሃገር ውስጥ በገፍ ገብተዋል በሚልም ስጋትዎን ይገልፃሉ፡፡ … ታዲያ በየት በየት በኩል አድርገው ነው ለውጡን ተቀብያለሁ የሚሉት? በቦሌ ወይስ በባሌ?

ውድ ጄኔራል፣ ‹እኔ ኒውትራል ልሁን ባልኩ ለምን ተነካሁ፣› እንዳይሉና እንዳያስቁኝ፡፡ ለመሆኑ፣ እርስዎስ ከነዚያኞቹ ጠባብ፣ አሮጌና ከፉ ‹ፖለቲከኞች› በምን በምን ይለያሉ? እንደኔ እንደኔ፣ በምንም! በሉ እንግዲህ፣ በጀመርኩት በጥልዬ ዘፈን ነገሬን ልቋጥርና ልሰናበትዎ፡፡

‹‹…ለሐሰት ያደረ ጊዜ ያቆረቁዛል፤

የዕውነት ምሰሶ መች ይነቃነቃል፡፡

ምርቱ እየነጠረ ግርዱ ሲንገዋለል፣

አለው ፍጹምነት ስው ከሰው መካከል፡፡…››

**********